# ውጪ እንብላ!




*(የፎቶ ባለቤት፡- Ryan Givens)*

## ምን ማለትህ ነው?

ወረርሽኙ እርስ በርስ በምንገናኝበት መንገድ ላይ ብዙ ለውጦችን አድርጓል። አንዳንዶቻችን በቤት ውስጥ ድጋሜ ለመመገብ ዝግጁ አይደለንም። ይህ ማለት ግን ማንም ሰው ከShoreline ታላቅ ሬስቶራንቶች መቅረት አለበት ማለት አይደለም! ብዙም ጥቅም ላይ ያልዋሉ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ወደ የመመገቢያ እድሎች ለመለወጥ ለማገዝ በከተማው አዳራሽ ያሉት ተወካዮችዎ ጠንክረው ይሰራሉ። ይህንን በሁለት-ደረጃ አካሄድ እንደምናሳካው ተስፋ እናደርጋለን። በመጀመሪያ በግል ይዞታ ላይ ባሉ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ መሥራት እንፈልጋለን። ይህንን ካደረግን በኋላ፣ ወደ የእግረኛ መንገድ የመመገቢያ ልምዶች እየተንቀሳቀስን ነው።

## ከተማዎ ከእርሶ መስማት ይፈልጋል!

ከዲሴምበር 16፣ 2021 ጀምሮ የእቅድ ኮሚሽኑን ውይይት በመመልከት በፍጥነት ይቀላቀሉ።

ፕረዘንቴሽኑን ይመልከቱ
[የስብሰባ ጥቅሉን ያንብቡ]
[የቪዲዮ ቅጂውን ይመልከቱ]

እባኮትን ለዝማኔዎች እዚህ ገጽ ላይ ያለውን የድር ቅጹ በመጠቀም ይመዝገቡ። ውይይቱ በሚመጣው የእቅድ ኮሚሽን ስብሰባ ላይ ይቀጥላል።

ማንኛውንም ሀሳቦች እና አስተያየቶች በስልክ ወይም በኢሜል እናበረታታለን፣ የእውቂያ መረጃውን በ"ያግኙን" ሳጥን ውስጥ ይመልከቱ።

## ይህን ለምንድነው የምናደርገው?

ወረርሽኙ በተከሰተበት ወቅት አንዳንድ የአካባቢያችንን ንግዶች ለመርዳት በሚደረገው ጥረት፣የእርስዎ የከተማ ምክር ቤት ሬስቶራንቶች ደንበኞቻቸውን በመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣በእግረኛ መንገዶች እና በሌሎች ውጪ የሆኑ የህዝብ ቦታዎች ደንበኞቻቸውን እንዲያስተናግዱ ለማድረግ ጊዜያዊ ደንቦችን አውጥቷል። እነዚህ ደንቦች ንግዶች መዘጋቶችን እና ሌሎች የኮቪድ-19 ገደቦችን እንዲቋቋሙ ተለዋዋጭነትን ሰጥተዋል።

የከተማዎ ምክር ቤት እነዚህን ደንቦች ሶስት ጊዜ ቢያራዝምም፣ ጁን 21፣ 2022 ጊዜው እንዲያበቃ ተዘጋጅተዋል። በShoreline ለሚገኙ ሰዎች በሙሉ በውጪ መመገብን ቋሚ እድል ለማድረግ ተስፋ እናደርጋለን። እባኮትን እነዚህን ሥርዓቶች ለማንበብ ነፃነት ይሰማዎ፡-

- ደንብ ቁ. 895 (የመጀመሪያ ጊዜያዊ ደንቦች)
- ደንብ ቁ. 917 (ሁለተኛ ማራዘሚያ)
- ደንብ ቁ. 936(ሶስተኛ ማራዘሚያ)
- {ደንብ ቁ. 952 (0ራተኛ እና በጣም የቅርብ ማራዘሚያ)

የአሁኖቹ ጊዜያዊ ደንቦች እንደሚከተለው ይሰራሉ፡-

| የግል መኪና ማቆሚያዎች | የህዝብ ቦታዎች |
|---|---|
| • የውጪ መቀመጫ ቦታ መመዝገቢያ ቅጽ ያስገቡ.<br>• ነጻ ነው!<br>• የግል የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላላቸው ሬስቶራንቶች የተፈቀደ | • ለ የቅድሚያ የቦታ ፍቃድይስገቡ<br>• ይሄም ነጻ ነው!<br>• የእግረኛ መንገዶችን፣ የመንገድ መኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ወይም ሌሎች የህዝብ ቦታዎችን መጠቀም ለሚፈልጉ ሬስቶራንቶች የተፈቀደ። |

## ይህ እንዴት ነው የሚሰራው?

ከተማዋ ለምን እንደዚህ ትመስላለች ብለው ጠይቀው ካወቁ፣ ከተማችን ማህበረሰቡ ምን እንደሚመስል የራሱ የሆነ ደንብ አላት። እነዚህ ደንቦች ምን ጥቅም ላይ እንደሚውሉ, የት እንደሚፈቀዱ እና ሕንፃዎች ምን እንደሚመስሉ የመሰሰሉ ነገሮችን ያካትታሉ። እነዚህን ደንቦች በShoreline የማዘጋጃ ቤት ኮድ ርዕስ 20 የልማት ኮድ ማግኘት ይችላሉ.

እነዚህ ህጎች ላይ ለውጦች ወይም ማሻሻያዎች ሲቀርቡ በእቅድ ኮሚሽኑ ይገመገማሉ፣ ይህም የሾርላይን ነዋሪዎች የበጎ ፈቃደኛ ቦርድ ሲሆን ለከተማው ምክር ቤት ጥቆማዎችን ያቀርባሉ። እርስዎ የተመረጡ መሪዎች እንደመሆናቸው፣ የከተማው ምክር ቤት በምን አይነት ህጎች እንደሚቀየሩ ይወስናል። ሁሉም የምርምር፣ የማስተባበር እና የዝግጅት ፐረዘንቴሽኖች የተዘጋጀው በአከባቢዎ የተመረጡ ተወካዮችን ስራ ለመስራት በተለያዩ የስራ መስኮች የተሰማሩ የርዕሰ ጉዳይ ባለሞያዎች በሆኑት የከተማው ሰራተኞች ነው።

ከማህበረሰብ አጋሮቻችን ጋር በምንሰራበት ጊዜ (ይህ እርስዎ የሚገቡበት ቦታ ነው)፣ የከተማው ሰራተኞች ይህንን እቃ በስተመጨረሻ በከተማው ምክር ቤት ግምት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ለዕቅድ ኮሚሽኑ ብዙ ጊዜ ለግምገማ እና

ለማጣራት ያቀርባሉ። አንዴ ምክር ቤቱ ስርዓቶቹ/ደንቦቹ ላይ ድምጽ ከሰጠ ህጎቹ ይጸድቃሉ ከዛም የከተማው ሰራተኞች የውጪ አገልግሎቱን በቋሚ መልኩ ይፈቅዳሉ።

**"ያግኙን" ሳጥን**

Cate Lee
ዋና እቅድ አውጪ
(206) 801-2557
clee@shorelinewa.gov

Kevin Bagwell
ተባባሪ እቅድ አውጪ
(206) 801-2551
kbagwell@shorelinewa.gov